አዋጅ ቁጥር --------------/2000

# የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና የማሕበራት አዋጅ

በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠውን የዜጎች የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ አዋጅ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማሕበራት አዋጅ ቁጥር -----/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር፤

   1/ "የበጀት ዓመት" ማለት በግሪጎሪያን አቆጣጠር ከጀንዋሪ 1 እስከ ዲሴምበር 31 ወይም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ያለው ዓመት ነው፤

   2/ "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "ኢትዮጵያ ማህበር" ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተመሰረተ፣ ሁሉም አባላቱ ኢትዮጵያውያን የሆኑ፣ የገቢ ምንጩ ከኢትዮጵያ የሆነ እና ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ነው፡፡ ሆኖም ከአጠቃላይ ገቢው ከ10 በመቶ የማይበልጠውን ከውጭ ምንጭ የሚያገኝ ከሆነ የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሆኖ ሊቆጠሩ ይችላል፡፡

   3/ "የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት በውጭ ሕግ መሰረት የቋቋመ ወይም የውጭ ዜጎች በአባልነት ያሉበት ወይም የገቢ ምንጩ ከውጭ የሆነ ወይም የውጭ ዜጎች የሚቆጣጠሩት የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፤

   4/ "የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር" ማለት ሁሉም አባላቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ፣ ከ10 በመቶ በላይ የሚሆነው የገቢ ምንጩ ከውጪ የሆነ እና በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ነው፤

   5/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትሕ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

   6/ "የሥራ መሪ" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማሕበሩን አስተዳደር በአጠቃላይ የሚቆጣጠር እና የሚመራ ሰው ነው፤

   7/ "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፤

   8/ "የሥራ ቦታ" ማለት የአንድ ሰው ሠነዶችና የሒሣብ መዛግብት የሚቀመጡበት ወይም አንድ ሰው ሥራውን የሚያካሂድበት ቦታ ነው፤

   9/ "ሕዝባዊ መዋጮ" ማለት በሕዝባዊ ወይም በሥራ ማስኬጃ ወይም በመኖሪያ ቦታዎች በመሄድ የሚገኘውን ገቢ ለበጎ አድራጎት ተግባሮች እንደሚያውለው ገልጾ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት በዋጋ ወይም በነጻ ለማሰባሰብ የሚደረግ ጥሪ

ማለት ሲሆን በሀይማኖት ወይም ለቀብር አገልግሎት ላይ በዋለ መሬት ወይም ሕንፃ ወይም አጠገባቸው ባለ መሬት ላይ የሚደረግ ጥሪን አያጠቃልልም፤

10/ "መተዳደሪያ ደንብ" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ የተቋቋመባቸዉን ወይም ሊያራምዳቸው የሚችሉ ዓላማዎች ወይም ሀብቱን በሥራ ላይ የሚያውልባቸው፣ የአባልነት እና የአመራር ቦታዎችን ለማግኘት የሚያበቁ መመዘኛዎችን፣ የአመራር ቦታ በሹመት ወይም በምርጫ የሚሰጥበት መንገድ፤ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ የሚተዳደርበት እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚሻሻሉበት መንገድና ሁኔታን ያጠቃልላል፤

11/ "የዘርፍ አስተዳዳሪ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 67 መሠረት የተሰየመ የፌዴራል አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ነው፤

12/ "ብዙሃን ማህበራት" ማለት የሙያ ማህበራትን፣ የሴቶች ማህበራትን፣ የወጣት ማህበራትንና ሌሎች ተመሳሳይ የኢትዮጵያ ማህበራትን ያካትታል::

3. የተፈጻሚነት ወሰን

1/ ይህ አዋጅ በሚለተሉት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

ሀ) ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች በሚሰሩ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት፤

ለ) በአንድ ክልል ብቻ የሚሠሩ ቢሆንም በኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት፤

ሐ) በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚሰሩ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት::

2/ ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

ሀ) በሃይማኖት ድርጅቶች፤

ለ) ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍና የውጭ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት፤

ሐ) የዕድርና የዕቁብ ማሕበራት::

## ክፍል ሁለት

## የበጎ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ኤጀንሲ

4. መቋቋም

1/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2/ ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል::

5. የኤጀንሲው አላማዎች

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲስፋፉና ተልዕኮዋቸውን በሕጉ መሠረት እንዲወጡ ማስቻልና ማበረታታት፤

2/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት አሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ መፍጥር፤

3/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በሕጉ መሠረት መሥራታቸውን መቆጣጠር::

**6. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት**

1/ ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ፈቃድ መስጠት፣ መመዝገብና መቆጣጠር፤

ለ) የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት የተሻለ አሠራር እንዲኖራቸው ማበረታታት፤

ሐ) ከሚያከናውናቸው ተግባራት ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች ማሰባሰብ፣ ማጠናቀርና፣ ማሰራጨት፤

መ) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ጋዜጣ ማሳተምና ማሰራጨት፤

ሠ) የመንግሥት አካላት እና የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት የሚሳተፉባቸው የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፤

ረ) ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችል የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

ሰ) ለምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርቡ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ጉዳይ ከሚመለከተው ዘርፍ አስተዳዳሪ ጋር በመመካከር መርምሮ መወሰን፤

ሸ) በአዋጅ ቁጥር 334/1995 (እንደተሻሻለ) ስለሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የተደነገገው ቢኖርም የዘለቄታ በጎ አድራጎትና የአደራ በጎ አድራጎት ንብረትን በማስመልከት የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ ተግባሮችን ማከናወን፤

ቀ) ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚጸድቀው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎችን መሰብሰብ፤

በ) የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

ተ) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በውክልና መስጠት፤

ቸ) ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈጸም::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ) የተመለከተው ቢኖርም ሚኒስትሩ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽህፈት ቤት በኤጀንሲው ቅጥር ግቢ ቅርንጫፍ እንዲከፍት ወይም ሠራተኞቹን እንዲመድብ ሊያዝ ይችላል::

**7. የኤጀንሲው አቋም**

ኤጀንሲው፣

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፣

2/ በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣ እና

3/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል::

**8. የቦርዱ አባላት**

1/ ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ ሰባት አባላት ይኖሩታል::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚሰየሙ የቦርድ አባላት መካከል ሁለቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ከማህበራት የተወጣጡ ይሆናል::

9. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1/ ከዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጋር ተያይዘው በሚነሱ የፖሊሲ ጉዳዮችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

2/ የበጎ አድራጐት ድርጅቶችና የማህበራት አስተዳደርን በተመለከተ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል፤

3/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ይግባኞችን መርምሮ ይወስናል፤

4/ በዚህ አዋጅ መሠረት በኤጀንሲው የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፤

5/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡለትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራትን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮችን መርምሮ ይወስናል::

10. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም እንዳስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል::

2/ በቦርዱ ስብሰባ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል::

3/ የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ የሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1/ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል::

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ለኤጀንሲው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ሠራተኞች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓለማዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኤንጀሲውን የሥራ መርሐ ግብርና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ መርሐ ግብር መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚደረጉ ማናቸውንም ግንኙነቶች በተመለከተ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል::

3/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል::

**12. በጀት**

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**13. የሂሳብ መዛግብት**

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በያመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት
## የበጐ አድራጐት ድርጅቶች

### ንዑስ ክፍል አንድ
### አጠቃላይ

**14. ትርጓሜ**

1. "የበጐ አድራጐት ድርጅት" ማለት ለበጐ አድራጐት ዓላማ ብቻ የተመሠረተና ለህዝብ ጥቅም የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡
2. "የበጎ አድራጎት ዓላማ" የሚከተሉትን ያካትታል፤
   ሀ) ድህነትን ወይም አደጋን መከላከል፣ መቀነስ ወይም ማስወገድ፤
   ለ) የኢኮኖሚ እድገትን እና የአካባቢ ጥበቃን ወይም ማሻሻልን ማፋጠን፤
   ሐ) የእንስሳት ደሕንነትን ማስፋፋት፤
   መ) ትምህርትን ማስፋፋት፤
   ሠ) ጤንነትን ወይም ሕይወት ማዳንን ማራመድ፤
   ረ) ጥበብን፣ ባሕልን፣ ቅርስን ወይም ሣይንስን ማዳበር፤
   ሰ) አማተር ስፖርትንና የወጣቶችን ደሕንነት ማስፋፋት፤
   ሸ) በዕድሜ፣ በአካልና አእምሮ ጉዳተኝነት፣ በገንዘብ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የተቸገሩትን መታደግ፤
   ቀ) የአገሪቱን የረጅም ጊዜ የልማት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማበረታታት፤
   በ) የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታት፤
   ተ) የብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዘቦች፣ የጾታና ሃይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፤
   ቸ) የሕጻናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፤
   ኀ) የግጭት አፈታትን ወይም እርቅን ማስፋፋት፤
   ነ) የፍትህና የህግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር፤
   ኘ) ሌሎች ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ የሚደነገጉ ዓላማዎች፡፡
3. ሕዝባዊ ጥቅም ይኖራል ተብሎ የሚቆጠረው፣
   ሀ) የበጐ አድራጐት ድርጅት ዓላማዎች አንድ ተለይቶ የሚታወቅ ጥቅም ለሕዝቡ የሚያስገኙ ሲሆን፣
   ለ) የበጐ አድራጐት ድርጅት ዓላማዎች ሊጠቀሙ የሚገባቸውን ሰዎች የማያገሉ ሲሆን፣ እና

ሐ) ለግለሰቦች ወይም ለድርጅቶች የሚያስገኘው የግል ጥቅም የድርጅቱ ዋና የሥራ ዓላማ በመሆኑ ሣይሆን በአጋጣሚና ድርጅቱ ዓላማውን በሚያሳካበት ጊዜ በተቀፅላነት የተገኘ ሲሆን፣

ብቻ ነው፡፡

4. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ዓላማዎችና የህዝብ ጥቅምን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(በ)፣ (ተ)፣ (ቸ)፣ (ኀ) እና (ነ) በተመለከቱት የበጎ አድራጎት ዓላማዎች ላይ መሰማራት የሚችሉት የኢትዮጵያ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ይሆናሉ፡፡

## 15. የበጐ አድራጐት ድርጅት ዓይነቶች

1. የበጐ አድራጐት ድርጅት፣

ሀ) የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅት፤

ለ) የበጐ አድራጐት ተቋም፣

ሐ) የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት፣ ወይም

መ)የበጐ አድራጐት ማህበር፣

ሆኖ ሊመሰረት ይችላል፡፡

2. በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል አምስት ስለበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጎ አድራጎት ሥራ ለመሠማራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አንዱን መመሥረትና በቅድሚያ የፈቃድና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሥራቸውን የሚያስተባብር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሕብረት ማቋቋም ይችላሉ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች

## 16. ትርጓሜ

"የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት አንድ የተለየ ንብረት በስጦታ ወይም በኑዛዜ ወይም በኤጀንሲው ትእዛዝ በዘላቂነትና በማይመለስ ሁኔታ ለበጐ አድራጐት ዓላማ ብቻ የሚውልበት ድርጅት ነው፡፡

## 17. ለምዝገባ ስለማመልከት

1. መሥራቹ በሕይወት ሳለ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባ የሚጠየቀው መሥራቹ በራሱ ወይም ለዚህ ጉዳይ በወከለው ሰው ብቻ ነው፡፡

2. መሥራቹ ከሞተ በኋላ ጥያቄው የሚቀርበው መሥራቹ አደራ በሰጠውና ይህን የተቀበለው ሰው ወይም የመሥራቹን ኑዛዜ በሚያስፈጽሙ ሰዎች ነው፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱት በማይኖሩበት ጊዜ ለዘለቄታ ንብረትን ለበጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ውል ያዘጋጁ፣ ምስክር የሆኑ ወይም ውሉን በአደራ ያስቀመጡ ሰዎች የምዝገባ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት ምዝገባ የመጠየቅ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ምዝገባውን ሳይጠይቁ የቀሩ እንደሆነ መሥራቹ ከሞተ ከሦስት ወር በኋላ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ማንኛውም ይመለከተኛል በሚል ሰው አመልካችነት ወይም በኤጀንሲው አነሳሽነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

5. ኤጀንሲው የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከፈለጉ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሞዴል መተዳደርያ ደንቦችን ያዘጋጃል፡፡

## 18. ንብረትን ለዘለቄታ ለበጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባርን መሻር

1. ለዘለቄታ ንብረትን ለበጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባር በኤጀንሲው ከመመዝገቡ በፊት መሥራቹ ሊሽረው ይችላል፡፡
2. የመሥራቹ ወራሾች የመሻር መብታቸውን ሊጠቀሙ የሚችሉት የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ እንዲመዘገብ ለኤጀንሲው ጥያቄ በቀረበ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ሳይመዘገብ ከቀረ ይሆናል፡፡

## 19. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አደረጃጀት

ማናቸውም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች ይኖረዋል፡፡

## 20. የሥራ አመራር ቦርድ ጥንቅር

1. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በመሥራቹ ወይም እርሱ በወከለው ሰው ካልተሾሙ ኤጀንሲው የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡
2. የቦርዱ አባል በማንኛውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አዲስ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡
3. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥር በምንም ዓይነት ቢሆን ከሦስት በታች ሊሆን አይችልም፡፡

## 21. የሥራ አመራር ቦርዱ ስልጣንና ተግባራት

1. የሥራ አመራር ቦርዱ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የበላይ አካል ይሆናል፡፡
2. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን የሚመራ ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ያሰናብታል፡፡
3. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ያስተዳድራል፡፡

## 22. የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባዎች

1. የሥራ አመራር ቦርዱ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተው መሠረት ይሰበሰባል፡፡
2. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ውሣኔዎችን የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡

## 23. ለቦርዱ አባላት የሚፈፀሙ ክፍያዎች

1. በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም በማናቸውም ሕግ ካልተወሰነ በስተቀር አንድ የቦርድ አባል ምንም ክፍያ አያገኝም፡፡
2. በቦርድ ስብሰባ ላይ ለመገኘት አንድ አባል ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን የሚደረግ የወጪ ማካካሻ እንደ ክፍያ አይቆጠርም፡፡

## 24. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባራት

የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፣

1. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ሥራ ይመራል፣ ድርጅቱን በመተዳደርያ ደንቡ መሠረት ያስተዳድራል፤
2. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፤
3. የሥራ አመራር ቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

4. የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራና የሂሣብ ሪፖርቶችን ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፤
5. የድርጅቱን ገቢ የሚያሳድጉ ሁኔታዎችን ያጠናል፣ በሥራ አመራሩ ቦርዱ ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በድርጅቱ ስም በተከፈቱ የባንክ ሂሣቦች ላይ ይፈርማል፤
7. ሌሎች በስራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ተያያዥ ተግባራት ያከናውናል::

25. <u>የኦዲተር ሥልጣንና ተግባራት</u>

የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ኦዲተር፣

1. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤
2. የድርጅቱን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በኢትዮጵያ ተቀባይነትን ባገኘ መመዘኛ መሠረት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል::
3. በዚህ አዋጅ የውጭ ኦዲተርን በተመለከተ የተደነገገው ቢኖርም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በማናቸውም ጊዜ የውጭ ኦዲተር ሊጠቀም ይችላል::

26. <u>ተጠቃሚዎችን ስለመወሰን</u>

መሥራቹ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችን በበቂ ሁኔታ ካልወሰነ ቦርዱ ከመሥራቹ ሀሣብ ጋር ይስማማል ብሎ በሚገምተው መልኩ ተጠቃሚዎችን ሊወስን ይችላል::

## <u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

## <u>የበጐ አድራጐት ተቋማት</u>

27. <u>የበጐ አድራጐት ተቋም</u>

1. የበጐ አድራጐት ተቋም ቁጥራቸው ቢያንስ ሶስት በሚደርሱ ሰዎች ለበጐ አድራጐት ተግባራት ብቻ የሚቋቋም የበጐ አድራጐት ድርጅት ነው::
2. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅትን አደረጃጀትን የሚመለከቱት የዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች ከአስፈላጊ ማስተካከያ ጋር ለበጐ አድራጐት ተቋም አደረጃጀትም ተፈጻሚ ይሆናሉ::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ የበጐ አድራጐት ተቋሙ አደረጃጀት በዚህ አዋጅ ክፍል አራት ስለማህበር አደረጃጀት በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት እንዲመራ ሊደነግግ ይችላል::

28. <u>የአባላት ኃላፊነቶችና ግዴታዎች</u>

1. እያንዳንዱ የበጐ አድራጐት ተቋም አባል ወይም አዲስ አባል ድርጅቱ እርሱ አባል በነበረበት ጊዜ ወይም አባልነቱ ካበቃ በኂላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሲፈርስ አባልነቱ ከማብቃቱ በፊት ለነበሩት የድርጅቱ እዳዎችና ኃላፊነቶች እንዲሁም ድርጅቱን የማፍረስ ሂደት የሚያስፈልጉ የአገልግሎት ዋጋዎችንና ወጭዎችን ለመሸፈን ከተወሰነ ጣሪያ በላይ ያልሆነ ገንዘብ ማዋጣት ይኖርበታል::
2. ኤጀንሲው የበጐ አድራጐት ተቋማት ለምዝገባ በሚቀርቡበት ወቅት ዋስትና ሊሰጡ የሚገባቸውን አነስተኛ የገንዘብ መጠን በሚያወጣው መመሪያ መወሰን ይችላል::

**29. ለምዝገባ ስለማመልከት**

የበጐ አድራጐት ተቋም የማቋቋም ዓላማ ያላቸው ሰዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 በተደነገገው መሠረት ለመመዝገብ ለኤጀንሲው ማመልከት አለባቸው፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት

## የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቶች

**30. ትርጓሜ**

"የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት" ማለት የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን በሚያቋቁመው ሠነድ መሠረት አንድ የተለየ ንብረት ለበጐ አድራጐት ዓላማ ብቻ እንዲውል በአደራ ጠባቂዎች የሚተዳደር ድርጅት ነው፡፡

**31. አመሰራረት**

1/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት በስጦታ ወይም በኑዛዜ ወይም በኤጄንሲው ትእዛዝ ሊቋቋም ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ስጦታ ወይም ኑዛዜ አግባብ ባላቸው የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል፡፡

3/ በስጦታ ወይም ኑዛዜ ውስጥ የሚገኙ በተዘዋዋሪ አመልካች አንቀጾች የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት ለማቋቋም በቂ ይሆናሉ፡፡

**32. የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት ቀጣይነት**

1/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ለተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል፡፡

2/ ላልተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ዘላቂና የማይሻር ይሆናል፡፡

**33. በአደራ ጠባቂዎቹ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ**

1/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት መስራች የሆነው ሰው አደራ ጠባቂዎቹን መሾም አለበት፡፡ እነዚህ አደራ ጠባቂዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 በተደነገገው መሠረት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለኤጀንሲው የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2/ አደራ ጠባቂዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት በተቋቋመ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3/ አደራ ጠባቂዎቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታው ወይም ኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር ሦስተኛ ወገኖችን የሚያካትት ማናቸውንም ድርጊት መፈፀም አይችሉም፡፡

**34. የአደራ ጠባቂዎች ብዛት**

1/ የአደራ ጠባቂዎች ብዛት በማናቸውም ምክንያት ከ3 ያነሰ እና ከ5 የበለጠ ሊሆን አይችልም፡፡ ከ3 ያነሱ ሰዎች ተጠቅሰው ከሆነ ይህን መመዘኛ ለማሟላት ኤጀንሲው ቀሪዎቹ የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

2/ ከ5 በላይ አደራ ጠባቂዎች ተጠቅሰው ከሆነ መሥራት የሚችሉና ፈቃደኝነት ያላቸው በቅድሚያ የተጠቀሱት 5 ሰዎች ብቻ አደራ ጠባቂ ይሆናሉ፡፡ ቀሪዎቹ ሰዎች ክፍት ቦታዎች ተፈጥረው ካልተሾሙ በስተቀር አደራ ጠባቂ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት አደራ ጠባቂዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ከሆኑ የአደራ ጠባቂዎች ብዛት ከ3 በታች እንዲሆኑ ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከሚሾሙት አደራ ጠባቂዎቹ ቢያንስ አንዱ መደበኛ ቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ መሆን አለበት፡፡

**35. <u>የአደራ ጠባቂዎች አሿሿም</u>**

1/ አደራ ጠባቂውን የሚሾመው የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ያቋቋመው ሰው ወይም በእርሱ የተወከለው ሰው ከሌለ ኤጀንሲው አደራ ጠባቂው የሚሾምበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

2/ የተሾመው አደራ ጠባቂ ውክልናውን አልቀበልም ካለ ወይም በማናቸውም ምክንያት አደራ ጠባቂነቱን ማከናወን ካልቻለ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት አዲስ አደራ ጠባቂ ይሾማል፡፡

**36. <u>የበጐ አድራጐት ድርጅትን በአደራ ጠባቂነት መሾም</u>**

1/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት የሚያቋቁም ሰው የበጐ አድራጐት ድርጅትን በአደራ ጠባቂነት ከሾመ የተሾመው ድርጅት ስራ መሪዎች የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ያስተዳድራሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የበጐ አድራጐት ድርጅት የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን በኑዛዜው፣ በስጦታው ወይም በኤጀንሲው ትእዛዝ በተወሰነው መሠረት ከሌሎች ስጦታዎች ወይም ዓላማውን ለማሳካት ከሚጠቀምበት ገቢ ለይቶ በመያዝ ያስተዳድራል፡፡

**37. <u>የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት አደረጃጀት</u>**

1/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትን የሚያቋቁም ሰው አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጅ፣ ገንዘብ ያዥ እና ኦዲተር ካልሾመ ወይም እነዚህኑ የሚሾም ሰው ካልወከለ አደራ ጠባቂዎቹ ከራሣቸው መካከል እነዚህን ይመርጣሉ፡፡

2/ አደራ ጠባቂዎቹ ይህን ምርጫ ያላደረጉ ከሆነ ወይም መወሰን ካልቻሉ ኤጀንሲው ይሾማል፡፡

3/ ከሦስት በላይ የሆኑ አደራ ጠባቂዎች ሲኖሩ ያልተሾሙት አደራ ጠባቂዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀት (1) መሠረት የተሾሙት በተሾሙበት ቦታ ካሉባቸው ኃላፊነቶች በተጨማሪ ሌሎች አደራ ጠባቂዎች ያሏቸው መብቶችና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡፡

4/ አደራ ጠባቂዎቹ ስብሰባቸውን የሚመራ ሊቀመንበር ከመካከላቸው ይመርጣሉ፡፡

**38. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደር</u>**

1/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደር በተመለከተ ከአደራ ጠባቂዎቹ ቢያንስ አንዱ በጽሑፍ እስካልተቃወመ ድረስ የአደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ የሌሎች አደራ ጠባቂዎች ስምምነት ሳያስፈልገው የማስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፡፡

2/ ከማስተዳደር ሥራዎች ውጭ ያሉና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቃውሞ የቀረበባቸው ውሣኔዎች ከአደራ ጠባቂዎች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱ በተገኙበት ስብሰባ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡

3/ የተለያዩ ሃሣቦች ከአደራ ጠባቂዎች ውስጥ እኩል ድጋፍ ያላቸው ሲሆኑ የመጨረሻው ውሣኔ የስብሰባው ሊቀመንበር በሚሰጠው ድምጽ ይወሰናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት በተሰጡ ውሳኔዎች የማይስማሙ አደራ ጠባቂዎች የልዩነት ሃሣባቸው በቃለ ጉባኤው ላይ እንዲመዘገብላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

5/ አደራ ጠባቂዎቹ በአደራ በጐ አድራጐቱ ስራ መሪነታቸው ለፈጸሚቸው ከሥልጣን በላይ የሆኑ ድርጊቶች በግል ኃላፊ ናቸው፡፡

39. <u>የአደራ ጠባቂዎች ሥልጣን</u>

1/ አደራ ጠባቂዎቹ በአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ላይ ያላቸው ሥልጣን የአንድ ባለንብረት ሥልጣን ነው፡፡

2/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር አደራ ጠባቂዎቹ ከኤጀንሲው ፈቃድ ውጭ ባለቤትነትን ለሌላ ሰው ሊያስተላለፉ አይችሉም፡፡

3/ አነስተኛ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አደራ ጠባቂዎች የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ንብረት ያለ ዋጋ ለሌላ ሊያስተላልፉ አይችሉም፡፡

40. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን ስለመወከል</u>

1/ አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ይወክላል፡፡ አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ በእርሱ ምትክ ድርጅቱን የሚወክለውን አደራ ጠባቂ ይመርጣል፤ እንዲሁም ማናቸውም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ጉዳዮች የሚከታተል ጠበቃ መወከል ይችላል፡፡

2/ አደራ ጠባቂዎቹ ከሥልጣን ወሰናቸው ሣያልፉ ለፈጸሚቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ተጠያቂ የሚሆነው የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ነው፡፡

41 <u>የማቋቋሚያ ሰነዱ ትእዛዞች</u>

1/ የአደራ ጠባቂው የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ካቋቋመው ሰነድ የተቀበላቸውን ግልጽ የሆኑ ትእዛዞች መከተል አለበት፤

2/ በንዑስ ቁጥር (1) የተደነገገው ቢኖርም በአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ተጠቃሚ ለሆነው ሰው ጥቅም የሚያስፈልግ ሆኖ የታየ እንደ ሆነ ከተባሉት ትእዛዞች ውጭ እንዲሠራ አደራ ጠባቂው ከኤጀንሲው ፍቃድ መጠየቅ ይችላል፡፡

42. <u>ለአደራ ጠባቂዎች የሚፈፀም ክፍያ</u>

1/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ወይም በማናቸውም ሌላ ሕግ ክፍያን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ከሌለ በቀር አደራ ጠባቂ ክፍያ የማግኘት መብት አይኖረውም፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ሁሉም አደራ ጠባቂዎች ክፍያ ሊፈጸም እንደሚገባ በጽሁፍ ሲስማሙ እና ኤጀንሲው ሲያፀድቅ በባለሙያነት የሠራ አንድ አደራ ጠባቂ ለአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ለሰጠው ወይም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን በመወከል ለፈጸማቸው ድርጊቶች ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሀብት ተመጣጣኝ ክፍያ ያገኛል፤

3/ ሆኖም አንድ አደራ ጠባቂ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ በግሉ ያወጣቸው ወጭዎችና ኃላፊነቶች እንዲተኩለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

43. <u>የአደራ ጠባቂዎች ኃላፊነት</u>

አደራ ጠባቂዎች በውክልና ድንጋጌዎች መሠረት ለአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችና እንደ ነገሩ ሁኔታ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ሲቀር ንብረቱን መቀበል ለሚገባቸው ሰዎች የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን መልካም አስተዳደር በሚመለከት ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

**44. <u>የአደራ ጠባቂው ሥራ መልቀቅ</u>**

1/ የአደራ ጠባቂው ሥራ የመልቀቅ ሃሣብ እንዳለው ስራውን ከመልቀቁ ከሁለት ወር በፊት ለሌሎች አደራ ጠባቂዎች ሣያስታውቅ ቢቀር ከዚህ የተነሣ በአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ኪሣራ ኃላፊ ይሆናል፤

2/ የአደራ ጠባቂው ሥልጣኑን ለሌላ አደራ ጠባቂ እስከሚያስተላልፍ ድረስ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፤

3/ አንድ አደራ ጠባቂ የሥራ መልቀቂያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በንዑስ ቁጥር (1) የተደነገገው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከማለፉ 1 ወር አስቀድሞ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ባቋቋመው ሰው ወይም ይህን ለመፈጸም ሥልጣን በተሰጠው ሰው፤ እነዚህ ባይኖሩ በኤጀንሲው አዲስ አደራ ጠባቂ ይሾማል፡፡

**45. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ማስያዝ</u>**

1/ የተጠቃሚዎች አበዳሪ የሆኑ ሰዎች  የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማናቸውንም ተጠቃሚው ሊያገኝ የሚገባውን አበል በማናቸውም ሁኔታ ማስያዝ አይችሉም፡፡

2/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ሲፈርስ ከንብረቱ ክፍል የተወሰነውን ለመውሰድ መብት ያላቸው ሰዎች አበዳሪዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ማስያዝ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ   በሚቀርበት ጊዜ ባለእዳውን መተካት ይችላሉ፡፡

**46. <u>የተጠቃሚዎች መብቶች</u>**

1/ ተጠቃሚዎች በአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ሠነድ መሠረት የሚገባቸው ጥቅም እንዲሰጣቸው የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን   ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

2/ ተጠቃሚዎቹ መብቶቻቸውን የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጠር አደራ ጠባቂው እንዲሻር ወይም ተገቢ የሆነ ዋስትና እንዲሰጥ ኤጀንሲውን መጠየቅ ይችላሉ፡፡

3/ ተጠቃሚዎቹ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ አካል በሆኑ ንብረቶች ላይ የማዘዝ ወይም የማስተዳደር አንዳች መብት የላቸውም፡፡

4/ በንዑስ ቁጥር (3) የተደነገገው ቢኖርም  እነዚህን ንብረቶች በሚመለከት የይርጋ ዘመን እንዲቋረጥ ማድረግን በመሣሰለው ሥራ መብቶቻቸውን የመጠበቅ ሥራዎችን ብቻ መፈጸም ይችላሉ፡፡

5/ በተጨማሪም ሦስተኛ ወገኖች እንዲያውቁት አንድን የሆነ ንብረት የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ንብረት አካል መሆናቸውን በማስታወቂያ መግለጽ ይችላሉ፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል አምስት</u>

## <u>የበጐ አድራጐት ማህበራት እና የበጐ አድራጐት  ኮሚቴዎች</u>

**47. <u>ትርጓሜ</u>**

1/ "የበጐ አድራጐት ማህበር" ማለት ለበጎ አድራት ዓላማ የተቋቋመ ማህበር ነው፤

2/ "የበጐ አድራጐት ኮሚቴ" ማለት ቁጥራቸው 5 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ከሕዝብ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ለበጐ አድራጐት ዓላማ ለመሰብሰብ  ሃሣብ ያላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡

**48. <u>የበጎ አድራጎት ማህበር</u>**

አግባብነት ያላቸው ማህበራትን እና የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ለበጐ አድራጐት ማህበር ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 49. የበጐ አድራጐት ኮሚቴዎችን ስለ ማጽደቅ

1/ የበጐ አድራጐት ኮሚቴዎች በኤጀንሲው ሳያፀድቁ ገንዘብ ወይም ንብረት ማሰባሰብ ወይም ማናቸውንም ድርጊት መፈጸም አይችሉም፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኮሚቴውን ለማቋቋም በሚደረጉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

3/ ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ሲያጸድቅ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 69 እና 70 ድንጋጌዎች በማገናዘብ መወሰን አለበት፡፡

## 50. የሂሣብ መግለጫ

1/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡

2/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተቋቋመው ከ1 ዓመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ጊዜው እንዳለቀ የሂሣብ መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡

## 51. የበጐ አድራጐት ኮሚቴ አደረጃጀት

1/ የበጐ አድራጐት ኮሚቴን የማፅደቅ ውሣኔ መስራች አባላት እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ኘሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥና ኦዲተር ዝርዝር ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

2/ ውሣኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ዓላማዎች እና ዓላማዎቹን የሚያሳካበትን ጊዜ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

3/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራዎች እንዴት መከናወን እንዳለባቸው መወሰን እና በኮሚቴው የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት መጠንና አጠቃቀሙን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 52. የአባላት ኃላፊነት

1/ ከበጎ አድራጎት ኮሚቴው እንቅስቃሴ ለሚመነጩ ግዴታዎችና ዕዳዎች አባላት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን በተመለከተ ማናቸውም ለጋሽ፣ አባል፣ ተጠቃሚ፣ ኤጀንሲው ወይም የዘርፉ አስተዳዳሪ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡

## 53. በቂ ያልሆነ ገንዘብና ንብረት

1/ በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት በኮሚቴው የታሰበውን ዓላማ ለማሣካት በቂ ካልሆነ ወይም ዓላማውን ማሳካት የማይቻል ከሆነ ይህ ገንዘብ ወይም ንብረት የኮሚቴው መቋቋም በፀደቀበት  ውሣኔ መሠረት በሥራ ላይ ይውላል፡፡

2/ በውሳኔው ውስጥ ይህን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ በኤጀንሲው ቁጥጥር ሥር ሆኖ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለተመሣሣይ የበጐ አድራጐት ዓላማ ይውላል፡፡

3/ ገንዘቡን ወይም ንብረቱን ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው የሰጡ ሰዎች መልሰው ሊወስዱት አይችሉም፡፡

## 54. ቀሪ ገንዘብና ንብረት

1/ በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ዓላማውን ለማሣካት አስፈላጊ ከሆነው በላይ ከሆነ ቀሪው ገንዘብ ወይም ንብረት ኮሚቴውን ባፀደቀው ውሣኔ መሠረት ሥራ ላይ ይውላል፡፡

2/ በውሳኔው ውስጥ ይህን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ኤጀንሲው የሚያዝበት ሆኖ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለተመሣሣይ የበጐ አድራጐት ዓላማ ይውላል፡፡

3/ ገንዘቡን ወይም ንብረቱን ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው የሰጡ ሰዎች መልሰው ሊወስዱት አይችሉም፡፡

**55. ወደ ዘላቂ በጐ አድራጐት ድርጅትነት ስለመለወጥ**

1/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ባፀደቀው ውሣኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ለአንድ ለተወሰነ ዘላቂ ዓላማ የሚውል ከሆነ ይህንኑ ዓላማ ለማሣካት ዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅት ይቋቋማል፡፡

2/ በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት የታቀደውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው እጅግ የበዛ ከሆነ፤ የኮሚቴው አባላት በዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ለመመዝገብ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ለኤጄንሲው ሊያመለክቱና ከተፈቀደላቸው ለምዝገባ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ማህበራት

**56. ትርጓሜ**

1/ "ማህበር" ማለት ዓላማው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ ሕዝባዊ፣ የሙያ ወይም የብዙሃን ማህበር፣ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ወይም ማንኛውም ሕጋዊ ዓላማዎች ያሉት የሰዎች ስብስብ ነው፡፡

2/ ማህበራት ሥራዎቻቸውን የሚያስተባብር የማህበራት ሕብረት ማቋቋም ይችላሉ፡፡

**57. የማሕበራት ሕጋዊ ሰውነት**

1/ ማህበራት በኤጄንሲው እንደተመዘገቡ ሕጋዊ ሰውነት ያገኛሉ፡፡

2/ የማህበር አባልነት ለሶስተኛ ሰው ተላልፎ አይሰጥም ወይም አይተላለፍም፡፡

**58. የማህበራት መብቶችና ግዴታዎች**

1/ ማንኛውም ማህበር የማህበሩን መስፈርት ለሚያሟላ አዲስ አባል ክፍት መሆን አለበት፡፡

2/ ማንኛውም ማህበር የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ነው፡፡

3/ የማንኛውም ማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው፡፡

4/ ማንኛውም ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ካልሆነ በቀር አባላትን ሊቀበልና ሊያሰናብት አይችልም፡፡

5/ አባልነቱ እንዲቋረጥ የሚደረግ ማንኛውም የማህበር አባል የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በሥራ አስፈጻሚው የመሰማት መብት አለው፡፡

6/ ማህበሩ የፌዴራል ባህሪ እና ስያሜ ያለው ከሆነ የሥራው ቦታና የአባላት ጥንቅር ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና ያለው መሆን አለበት፡፡

7/ ኢትዮጵያውያን ብዙሃን ማህበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በምርጫ ሂደት በተለይም ትምህርታዊ ሴሚናሮችን በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በማዘጋጀት፣ የተወዳዳሪዎችን ፕሮግራም በመረዳት፣ የምርጫ ሂደቶችን በመታዘብና ከምርጫ አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር ረገድ በንቃት መሳተፍ ይችላሉ፡፡

8/ የማንኛውም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው አባል ጥያቄ የሚሻሻል መሆን አለበት፡፡

**59. የማሕበራት አደረጃጀት**

1/ የማንኛውም ማሕበር አደረጃጀት በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ማንኛውም ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ኦዲተር የያዘ መሆን አለበት፡፡

3/ የማህበሩ ኦዲተር በማህበሩ የስራ መሪነት ቦታ ሊይዝ አይችልም፡፡

**60. የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባራት**

የማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፣

1/ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፤

2/ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የማሕበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፤ ክፍያውን ይወስናል፤

3/ በማህበሩ የፖሊሲና ስታራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤

4/ በማህበሩ ሌሎች አካላት ሥልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፡፡

5/ የማሕበሩን መፍረስ ይወስናል፤

6/ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

**61. ከጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች መለየት**

1/ የተለየ ሃሳብ ያለው የማህበር አባል የልዩነት ሃሳቡን በቃለ-ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል፡፡

2/ ማናቸውም የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የአገሪቱን ሕግ፣ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን ይጥሳል ብሎ ሲያምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት ይችላል፡፡

**62. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች**

1/ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች በማሕበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተደነገገው መሠረት ይካሄዳሉ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሊቀመንበሩ በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ ከሆነ ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካይነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

3/ የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከሆነ ኤጀንሲው የጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር የሚሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል፤

4/ የጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ስብሰባ ለመጥራት ሁሉም ሊያውቀው የሚችል ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፤

5/ የማህበሩ ምልዐተ ጉባኤ በመተዳደሪያ ደንቡ በተወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡ ይህን የሚመለከት ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የስብሰባው አብዛኛው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል፡፡ ሆኖም መተዳደሪያ ደንቡ ከማህበሩ አባላት ከ50% በታች ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል ብለው መደንገግ አይችልም፡፡ ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በሚቀጥለው ሦስተኛ ስብሰባ ከአባላቱ 50% ባይገኙም በኤጀንሲው ውሳኔ ምልዓት ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

6/ የጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ:: ድምጽ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል:: የማሕበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተመረኮዘ መሆን አለበት::

7/ በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም::

63. <u>የኦዲተር ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኦዲተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር አለው፤

1/ የማህበሩን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤

2/ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነትን ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት የድርጅቱን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል፤

3/ በዚህ አዋጅ ስለ ውጭ ኦዲት የተደነገጉት ቢኖሩም ማሕበሩ በማንኛውም ጊዜ በውጪ ኦዲተር ሊጠቀም ይችላል::

64. <u>አባላትን የሚመለከቱ መረጃዎች</u>

1/ የማሕበሩ የሥራ መሪዎች የአባላቱን ዝርዝር ጉዳዮች ይመዘግባሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ሲጠየቁ ለኤጀንሲው ያቀርባሉ::

2/ ከማሕበራት የሚፈለጉ መረጃዎች ዝርዝር ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት አመሰራረት፣ ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ</u>

### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

### <u>የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት አመሰራረት</u>

65. <u>አመሰራረት</u>

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት በዚህ ሕግ የተቀመጠውን መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ እንደተመሠረቱ ይቆጠራል::

2/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በተመሠረተ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለምዝገባ ማመልከት አለበት::

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በቂ ምክንያት መኖሩን ካሳየ የጊዜ ገደብ ቢያልፍም ለምዝገባ የሚያመለክትበትን ጊዜ ኤጀንሲው እስከ ሦስት ወር ሊያራዝም ይችላል::

66. <u>የመመስረት ውጤት</u>

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በመመስረታቸው ብቻ ሕጋዊ ሰውነት አይኖራቸውም::

2/ የተመሰረተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሕጋዊ ሰውነት ሲያገኝ መብቶቹና ግዴታዎቹ ወደ ተመዘገበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይተላለፋሉ::

3/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበራት ከመመዝገባቸው በፊት የሚያሰባስበው ገንዘብ ወይም ንብረት ከብር ሃምሳ ሺህ በላይ ሊሆን አይችልም::

4/ በሕግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ያልተመዘገበ የተመሠረተ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እንዲቋረጥ ምክንያት ይሆናል::

**67. <u>የዘርፍ አስተዳደሪዎች</u>**

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68 የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባሮች የሚኖሯቸው አግባብነት ያላቸው የፌዴራል አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በዘርፍ አስተዳዳሪነት በሚኒስትሩ ይሰየማሉ።

2/ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በአንድ የተወሰነ የዘርፍ አስተዳዳሪ የማይሸፈን ወይም ከአንድ በላይ የዘርፍ አስተዳዳሪን የሚመለከት ከሆነ ኤጀንሲው የዘርፍ አስተዳዳሪ ይሆናል።

3/ ማናቸውም የዘርፍ አስተዳዳሪ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ለእርሱ ተጠሪ ለሆኑ የፌዴራል መንግስት አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**68. <u>የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ሥልጣንና ተግባር</u>**

1/ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ፈቃድና ምዝገባ ሂደት ለኤጀንሲው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

2/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚገመግሙና አስተያየት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይመድባል፤

3/ በማቋቋሚያ ሕጉ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

4/ የዘርፍ አስተዳዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የወሰደውን እርምጃ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ያሳውቃል፤

5/ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ከማህበራት ሥራዎች ህብረተሰቡ የላቀ ተጠቃሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው ሊከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ያወጣል።

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ምዝገባ</u>

**69. <u>ምዝገባ</u>**

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ማመልከቻ ሲቀርብለት በዚህ አዋጅ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አመልካቾቹን በበጐ አድራጐት ድርጅትነት ወይም በማህበርነት በመመዝገብ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

2/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ፎርም መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማሕበሩን ግብ፣ አላማና ሥራ የሚመለከቱ መግለጫዎችን የያዘ ሆኖ ከሚከተለት ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

ሀ) የበጎ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና እንደአግባብነቱ የዘላቂታ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያቋቋመው ሠነድ ቅጂ፤

ለ) እንዳስስፈለጊነቱ ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው ለሎች ሠነዶች።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች በተጨማሪ ውጪ አገር የተመሰረተ የበጐ አድራጐት ድርጅት የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፤

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መቋቋሙን የሚያሳይ ከተቋቋመበት አገር የተሰጠውን በአግባቡ የተረጋገጠ ሰነድ፤

ለ) ሥልጣን ያለው የድርጅቱ አካል ድርጅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠራ ያሳለፈው በአግባቡ የተረጋገጠ ውሣኔ፤

ሐ) ኢትዮጵያ ከሚገኝ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የተቋቋመበት አገር ኤምባሲ ወይም ኤምባሲ ከሌለ ከተቋቋመበት አገር ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

መ) ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

ሠ) የአገር ውስጥ ተወካዩ የተሰጠው በአግባቡ የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን::

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ሲቀርብ ተገቢው የምዝገባ ክፍያ መፈጸም አለበት::

**70. <u>የምዝገባ ጥያቄን ስላለመቀበል</u>**

ኤጀንሲው ከሚከተሉት አንዱ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን አይመዘግብም፤

1/ ሊቋቋም የታሰበው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር መተዳደርያ ደንብ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፤

2/ ሊቋቋም የታሰበው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሕገ-ወጥ ለሆነ፣ የሕዝብን ሠላም ለሚያደፈርስ ወይም የኢትዮጵያን ደህንነትና መረጋጋት ለመጉዳት መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖር፤

3/ የምዝገባ ማመልከቻው የዚህን አዋጅ ወይም በዚሁ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ድንጋጌዎች የማያሟላ ሲሆን፤

4/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ የሚመዘግብበት ስም ከሌላ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም ከማንኛውም ሌላ ተቋም ስም ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ወይም የሕዝብን ሞራል ወይም ሕግን የሚቃረን ሲሆን፤

5/ የማሕበሩ ስያሜ አገር አቀፋዊ ወይም ፌዴራላዊ ሆኖ የአባላት ጥንቅር ወይም የሥራ ቦታው ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና የሌለው ከሆነ::

**71. <u>በሥራ መሪነት መሥራት የማይችሉ ሰዎች</u>**

ማናቸውም ሰው በአንድ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም በእነዚሁ ቅርንጫፎች በሥራ መሪነት መሥራት የማይችለው፤

1/ ማጭበርበርን ወይም ሀቀኝነት የጎደለውን ድርጊት በሚያካትት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቶ ከሆነ፤

2/ በማናቸውም ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቶ የሲቪል መብቱን የተገፈፈና መብቶቹም ያልተመለሱለት ከሆነ፤

3/ በፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ከችሎታ ማጣት የተነሳ መሥራት የማይችል ከሆነ፤

4/ በፍርድ ክልከላ የተደረገበት ከሆነ፤

5/ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሌለና አለመኖሩ ለበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ ትክክለኛ አስተዳዳር እንቅፋት የሚሆን ከሆነ::

**72. <u>የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት መዝገብ</u>**

1/ ኤጀንሲው ማንኛውንም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበርን በሚመለከት በየጊዜው የሚወስናቸው ዝርዝሮች የሚመዘገቡበት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት መዝገብ ይይዛል፤

2/ የእንዲህ ዓይነት ሠነድ ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ በኤጀንሲው ዳይሬክተር ትክክለኛ ቅጂ ለመሆኑ የተመሠከረ ከሆነና የኤጀንሲው ማሕተም ከተደረገበት በማናቸውም የክርክር ሂደቶች በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል፤

3/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት መዝገብ በኤሌክትሮኒክ መልክ ጨምሮ ኤጀንሲው አግባብ ነው ብሎ በሚገምተው መንገድ ተዘጋጅቶ ይቀመጣል፡፡

4/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡትን እንዲሁም የታገዱትንና ከመዝገብ የተሠረዙትን የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ዝርዝር በጋዜጣ ያወጣል፡፡

**73. <u>የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ቅርንጫፍ</u>**

1/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር አስቀድሞ ኤጀንሲውን በማሳወቅ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚከፈት ቅርንጫፍ የሚሰጠው ሥልጣን ራሱን የቻለ የሚያደርገው ወይም የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ በቂ ቁጥጥር እንዳያደርግበት የሚያደርገው ሊሆን አይገባም፡፡

3/ አንድ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር አስቀድሞ ኤጀንሲውን ሳያሳውቅ ቅርንጫፍ ቢያቋቁም ይህ ቅርንጫፍ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 104 በተሰጠው ትርጉም መሠረት እንደ ሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ተደርጐ ይቆጠራል፡፡

**74. <u>ስያሜ፣ የሥራ ቦታ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ስለመለወጥ</u>**

1/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ስያሜውን ወይም የሥራ ቦታውን ከለወጠ ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ካሻሻለ ለውጡ ወይም ማሻሻያው ለኤጀንሲው አቅርቦ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 መሠረት ማስመዝገብ አለበት፡፡

2/ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ከተመዘገበ በኋላ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (3)፣ (4) ወይም (5) የተደነገገው በማናቸወም ምክንያት ሳየከበር መታለፉ ከተረጋገጠ ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል ወይም ጉደለቱ እንዲታረም ሊያዝ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተፈጸመ የስም ለውጥ የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን ማናቸውንም መብቶች ወይም ግዴታዎችን አይነካም፡፡ በቀድሞ ስሙ በእርሱ ወይም በራሱ ላይ ቀጥለው ወይም ተጀምረው የነበሩ ክርክሮች በአዲሱ ስም ይቀጥላሉ ወይም ይጀመራሉ፡፡

**75. <u>በምልክቶች ስለመጠቀም</u>**

1/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ለኤጀንሲው አቅርቦ ሳያስመዘግብ ማናቸውንም አርማ መጠቀም አይችልም፡፡

2/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበለትን ዓርማ ለመመዝገብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 የተደነገጉትን የምዝገባ መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

**76. <u>የምስክር ወረቀትን፣ ስያሜንና ምልክቶችን በይፋ ስለ ማሣየት</u>**

1/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን በዋናው መሥሪያ ቤትና ግልባጩን በየቅርንጫፎቹ ለማናቸውም ጉብኚ ሊታይ በሚችል ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

2/ አንድ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የማስታወቂያ ሠሌዳ የሚጠቀም ከሆነ ኤጀንሲው በመመሪያ የሚወስናቸውን ዝርዝሮች ሰሌዳው ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፤

**77. <u>ፈቃድ ስለማሳደስ</u>**

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 79 እና 81 መሠረት አመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫዎችን የማቅረብ ግዴታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃዳቸውን በየሦስት ዓመቱ ማሳደስ አለባቸው፡፡

2/ ፈቃድ የሚታደሰው በፈቃድና ምዝገባ ሰርተፊኬቱ ላይ የተገለፀው ጊዜ የሚያገለግልበት የመጨረሻ ቀን ካለፈ በኋላ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ነው፡፡

3/ ኤጀንሲው፣

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የስራ አፈጻፀምና የኦዲት ሪፖርቶች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን፣ እና

ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወይም በኤጀንሲው የተሰጡ ትዕዛዞችን ወይም የራሱን መተዳደሪያ ደንብ ያልጣሰ መሆኑን፣

ሲያረጋግጥና አስፈላጊው የመሳደሻ ክፍያ ከፈተመ በኋላ ፈቃዱን ያድሳል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት

## ሂሣብ እና ሪፖርቶች

**78. የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ**

1/ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የስራ መሪዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴዎች የሚያብራራ እና በማናቸውም ጊዜ ሊያሣይ የሚችል የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው፤

2/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሂሣብ ሰነዶች የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የተቀበለውን ጠቅላላ ገንዘብና ያወጣውን ወጪ፣ የወጪውን ምክንያት፣ ሀብትና ዕዳ ያካተቱ መሆን አለባቸው፤

3/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ስሙ ካልተገለፀ ሰው ልገሳ መቀበል አይችሉም፡፡ በማናቸውም ጊዜ የለጋሹን ማንነት በግልጽ የሚያመለክቱ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው፤

4/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት የተዘጋጁ የሂሳብ ሰነዶችን ሰነዶቹ የተዘጋጁበት የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ የሂሣብ ዓመት ካለቀ በኋላ ቢያንስ ለ5 ዓመታት ጠብቀው ማቆየት አለባቸው፡፡

5/ ኤጀንሲው ሰነዶቹ እንዲወድሙ ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገዱ በጽሁፍ ካልፈቀደ በስተቀር ከሂሳብ ሰነድ ጋር በተያያዘ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (4) የተገለጸው አምስት ዓመት ከማለቁ በፊት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሕልውና ካከተመ የሂሳብ ሰነዶቹን ጠብቆ የማቆየት ግዴታ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ቀሪ የስራ መሪዎች ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፡፡

**79. ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ**

1/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛ ዎች መሰረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ለኤጀንሲው በአድራሻ መላክ አለበት፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የሚያንቀሳቅሱት ገንዘብ ከብር 50,000.00 የማይበልጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ገቢን፣ ወጪን፣ ሃብትንና ዕዳን የሚያመለክት መግለጫ ብቻ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

3/ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የተዘጋጀ የሂሣብ መግለጫና ተያያዥ ሰነድ የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ጠብቀው ይቆያሉ፡፡

**80. <u>ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ ስለማድረግ</u>**

1/ የማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሂሣብ በየዓመቱ በተመሰከረለት ኦዲተር ወይም የውስጥ ኦዲተር ወይም ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር መመርመር አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በውጭ ኦዲተር የመመርመር ግዴታ የሚኖርበት አግባብነት ባለው የበጀት ዓመት ቀድሞ ያለው የበጀት ዓመት ሂሳብ የዓመቱ በጀት ከብር 100,000.00 የሚበልጥ ሲሆን ነው፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም ዓይነት የሂሳብ ምርመራ በማንኛውም ጊዜ በውጭ ወይም በውስጥ ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር ሊመረመር ይችላል፡፡

4/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ሂሣብ ዓመቱ ባለቀ አምስት ወራት ውስጥ ካልተመረመረ ወይም በውጭ ኦዲተር ማስመርመር የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲው ኦዲተር ሾሞ ማስመርመር ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በኤጀንሲው በተሾመው ኦዲተር ለተከናወኑ ማናቸውም የኦዲት ሥራዎች ወጭ የሚከፍለው የሚመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ የስራ መሪዎቹ ይሆናሉ፡፡

**81. <u>ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት</u>**

1/ የሥራ መሪዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም የማሕበሩን የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና ክንዋኔዎች ሪፖርትና አስፈላጊ መረጃ በማዘጋጀት ለኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሪፖርት በሥራ መሪዎቹ ለኤጀንሲው የሂሣብ ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም ኤጀንሲው በማናቸውም ልዩ ምክንያት በሚጠይቀው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለባቸው፡፡

3/ ማንኛውም የሥራ ክንውን ሪፖርት ለኤጀንሲው ሲደረግ የሂሣብ መግለጫ አብሮ መያያዝ አለበት፡፡

**82. <u>ዓመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ክፍት ስለማድረግ</u>**

በኤጀንሲው ዘንድ የሚገኝ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የዓመት ሪፖርት ወይም ሌላ ሠነድ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ወይም በኤጀንሲው ወይም በሚመለከተው የዘርፍ አስተዳዳሪ ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቱ እና ማህበሩ ውሳኔ በማናቸውም አመቺ ጊዜ ለሕዝብ ክፍት ሊደረግ ይችላል፡፡

**83. <u>ለሌሎች ሰዎች ሪፖርት ስለማድረግ</u>**

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የማህበሩ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት አካላት በተጨማሪ ለሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች የሂሳብ መዛግብት፣ የኦዲት ሪፖርቶች እና ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብን አይከለክልም፡፡

**84. <u>የባንክ ሂሳብ ስለማስታወቅ</u>**

የበጎ አድራት ድርጅት ወይም የማህበር መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የባንክ ሂሳብ ከሚፈለገው ዝርዝር ጋር ለኤጀንሲው በየዓመቱ እና በተጠየቁ ጊዜ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት

## የበጐ አድራጐት ድርጅቶችንና ማሕበራትን ስለመቆጣጠር

**85. ምርመራ የማድረግ ሥልጣን**

1/ ኤጀንሲው በየጊዜው ለአጠቃላይ ወይም ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን ወይም ማሕበራትን ወይም የተወሰኑ ወይም አንድ ዘርፍ የሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን ወይም ማሕበራትን የተመለከተ ምርመራ ሊያካሄድ ይችላል፡፡

2/ ለእንዲህ ዓይነት ምርመራ ጉዳይ ኤጀንሲው ማናቸውንም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም የሥራ መሪ ወይም ሠራተኛ፤

ሀ) የሚያውቀውን ወይም መረጃ ሊያገኝ የሚያስችለው ምክንያታዊ ግምት ኖሮ ምርመራው የሚካሄድበትን ጉዳይ በተመለከተ ሂሣብና መግለጫ በጽሁፍ እንዲሰጥ፣ ጉዳዩን በተመለከተ ለቀረበለት ጥያቄ ወይም ምርመራ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጥ፤

ለ) በምርመራው ሂደት መመርመር ያለበትን ማናቸውንም ጉዳይ በተመለከተ በእጁ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያሉትን ሠነዶች ቅጂ እንዲሰጥ፤ እና

ሐ) በተወሰነ ጊዜና ቦታ በመገኘት ማስረጃ ወይም ሠነዶችን እንዲያቀርብ፣

ሊያዝ ይችላል፡፡

3/ ኤጀንሲው ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ከሕዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን፣ ከመንግሥት አካላት የሚቀርቡ ሪፖርቶችን እና ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ከማሕበራት ከራሣቸው የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ጨምሮ ማናቸውንም የመረጃ ምንጭ ሊጠቀም ይችላል፡፡

**86. ሠነዶች እንዲቀርቡ የማዘዝና ሪከርዶች እንዲመረመሩ የማድረግ ሥልጣን**

1/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል ከአንድ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም የሥራ መሪ ወይም ሠራተኛ፤

ሀ) አንድን የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የሚመለከት በይዞታው ሥር ያለ ማንኛውንም መረጃ በጽሁፍ ወይም በቃል ለኤጀንሲው እንዲሰጥ፤ ወይም

ለ) የሠነዱን ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ ለኤጀንሲው  እንዲሰጥ፤ ወይም

ሐ) ሠነዱ የአንድ ፍርድ ቤት ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሪከርድ ወይም ሠነዶች አካል ካልሆነ በስተቀር ሠነዱን ራሱን ለምርመራ ለኤጀንሲው እንዲሰጥ፣

በትእዛዝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ ኤጀንሲው በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተቀበላቸውን ማናቸውንም ግልባጮች ወይም የሠነድ ክፍሎች ያለ ክፍያ የማግኘት ሥልጣን አለው፡፡

**87. ስብሰባዎችን ስለማስታወቅ**

ማንኛውም ማሕበር የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ከሰባት የሥራ ቀናት አስቀድሞ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ ለኤጀንሲው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**88. የበጐ አድራጐት ሥራዎችን ስለማስተባበር**

የዘርፍ አስተዳደሪ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችንና የዘርፍ አስተዳዳሪውን የጋራ ግቦች ለማሣካት የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይችላል፡፡

**89. _መረጃ ስለመግለጽ_**

በሌሎች ሕጐች በግልጽ የተደረጉት ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው ወይም የዘርፍ አስተዳዳሪው ሥራዎቹን በሚገባ እንዲያከናውን ለማስቻል ወይም ለመርዳት ማንኛውም ሰው ያገኛቸውን ማናቸውንም መረጃ ለኤጀንሲው ወይም ለዘርፍ አስተዳዳሪው መግለጽ ይችላል።

**90. _ስለአስተዳደራዊ ወጪዎች ገደብ_**

1/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት በየበጀት ዓመቱ የሚያወጣው አስተዳደራዊ ወጪ ዓላማውን ለማስፈጸም ከሚያወጣው አጠቃላይ ወጭ ከ30ን መብለጥ የለበትም።

2/ ከጠቅላላ ገቢው ከ80 በመቶ በላይ ለተቋቋመበት ዓላማ ለሚያውል የበጎ አድራጎት ድርጅት መንግሥት የተለያዩ ማበረታቻዎችን ሊያደርግ ይችላል።

**91. _የውጭ ዜጎችን ስለ መቅጠር_**

1/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሥራ ፈቃድ ያልተሰጠውን የውጪ ዜጋ መቅጠር አይችልም።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የውጭ የበጐ አድራጐት ድርጅት የውጭ ዜጋን የሀገር ውስጥ ተወካይ አድርጎ ለመመደብ ገደብ አይኖርበትም።

**92. _የንብረት ጥበቃ_**

ኤጀንሲው ማንኛውንም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር በተመለከተ በሚያደርገው ክትትል ወይም ምርመራ ተገቢ ያልሆነ የሥራ አመራር ወይም ድርጊት መፈጸሙን ሲያረጋግጥና የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ንብረት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፤

1/ ተገቢ ላልሆው ሥራ ሃላፊ የሆነውን የሥራ መሪ ማገድና ሥልጣን ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አካል ተተኪ እንዲመድብ ያዛል፤

2/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የአሠራር ሥርዓቱን እንዲያሻሻል ያዛል፤

3/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ እስከሚያደረግ ድረስ፣

ሀ) ያለ ኤጀንሲው ፈቃድ የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን የተወሰኑ ግዴታዎች ውስጥ የሚያስገቡ ውሎች እንዳይደረጉ ወይም የተወሰኑ ዓይነት ክፍያዎች እንዳይፈጸሙ ያግዳል፤

ለ) የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ንብረት በይዞታው ስር ያለን ሰው ወይም ባለዕዳን ያለ ኤጀንሲው ፈቃድ ንብረቱን እንዳይመልስ ወይም እዳውን እንዳይከፍል ያግዳል።

**93. _የስራ መሪዎችን ስለ ማንሳትና መተካት_**

1/ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይ የማህበር መሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 71 ከተመለከቱት መመዘኛዎች አንዱን ያጓደለ እንደሆነ ሥልጣን ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አካል እንዲነሳና በሌላ እንዲተካ እንዲደረግ ኤጀንሲው ያዛል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የሥራ መሪ በሰላ እስኪተካ ድረስ ከኃላፊነት እንዲታገድ ኤጀንሲው ሊያዝ ይችላል።

## 94. ፈቃድ ስለማገድና ስለመሰረዝ

1/ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74(2) መሠረት የተለለፈውን የኤጀንሲውን ተዕዛዝ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይፈጽም ከቀረ፣

ለ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወይም በኤጀንሲው የተሰጡ ትዕዛዞችን ወይም የራሱን መተዳደሪያ ደንብ የጣሰ እንደሆነ፣

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለኤጀንሲው ማቅረብ የሚገባቸውን መረጃዎች በወቅቱ ያላቀረበ እንደሆነ፣

ጉድለቶቹን እስከሚያስተካክል ድረስ ፈቃዱ በኤጀንሲው ሊታገድ ይችላል፡፡

2/ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፣

ሀ) የተመዘገበው በማታለል ወይም በማጭበርበር ከሆነ፣ ወይም

ለ) ሕገ ወጥ ለሆነ ዓላማ፣ ወይም የሕዝብን ሠላምና የአገርን ደህንነት ለሚጎዱ ዓላማዎች ውሎ ከሆነ፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለእግድ ምክንያት የሆኑትን ጉደለቶች ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፣ ወይም

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 77 መሠረት ፈቃዱን ካላሳደሰ፣

ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

## 95. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መፍረስ

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያፈርስ ይችላል፤

ሀ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሥልጣን ያለው አካል በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት እንዲፈርስ ሲወስን፤

ለ) የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 94 መሠረት በኤጀንሲው ሲሠረዝ፤ ወይም

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መፍረሱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲወሰን፡፡

2/ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የማህበር የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ይሆናል፤

ሀ) በወንጀል ሕግ ወይም በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የወንጀል ድርጊቶች ከፈጸመ፤ ወይም

ለ) የጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዕዳውን የመክፈል ችሎታ የሌለው ሲሆን፡፡

## 96. የመፍረስ ውጤት

1/ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር እንዲፈርስ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ፤

ሀ) ንብረቱ ወዲያውኑ የማፍረሱ ውሳኔ በተሰጠበት ትእዛዝ ወይም ውሳኔ የማፍረስ ሂደቱን እንዲያከናውን በተሾመው ሂሣብ አጣሪ ኃላፊነት ስር ይሆናል፤

ለ) ሂሣብ አጣሪው የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን እዳዎችና ኃላፊነቶች እንዲሁም የማፍረስ ሂደቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተጠናቀው ከተከፈሉ በኋላ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ቀሪ ገንዘብ ወይም ንብረት ካለ ተመሣሣይ ዓላማ ላለው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ለማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር እንዲተላለፍ በኤጀንሲው ትእዛዝ ይሰጣል፤

2/ የፈረሰ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበርን የሂሣብ አጣሪ መሾም በተመለከተ ኤጀንሲው ወይም ፍርድ ቤት የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ የሥራ መሪዎችን ወይም ማኛውንም ሰው ሊሾም ይችላል።

3/ ሂሳቡ በመጣራት ላይ ያለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከዓላማው ጋር የተያያዙና ሊቋረጡ የማይችሉ ሥራዎችን ኤጀንሲውን በማስፈቀድ ለማጠናቀቅ ካልሆነ በስተቀር ከሂሳብ ማጣራቱ ወጭ ሌላ ተግባር ማከናወን አይችልም።

4/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሂሳብ ማጣራት ሥራዎች ተጠናቀው ምዝገባው እስከሚሠረዝ ድረስ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቆያል።

## ክፍል ስምንት

## ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል

### 97. ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል የሚፈፀምባቸው ሁኔታዎች

1/ የበጐ አድራጐት ስጦታ የመጀመሪያ ዓላማ ሊለወጥ የሚችልባቸውና የተሰጠው ሙሉ ንብረት ወይም ከፊሉ ለሌላ ተቀራራቢ ዓላማ እንዲውል በሚከተሉት ሁኔታዎች ይፈጸማል፤

ሀ) የመጀመሪያ ዓላማ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሳካ ወይም የማይሳካ ወይም ሊሳካ የማይችል ሲሆን፤

ለ) ስጦታው ለመጀመሪያ ዓላማ ካለው ንብረት ከፊሉ ብቻ በጥቅም ላይ እንዲውል የሚያመለክት ሲሆን፤

ሐ) የስጦታው መንፈስ ሳይነካ በስጦታው መሠረት ያለው ንብረት እና ለተመሣሣይ ዓላማ የሚውል ሌላ ንብረት ቢቀናጁ አመቺ በሆነ ሁኔታ የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለጋራ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሲሆን።

2/ የዘላቂ በጐ አድራጐት ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ማቋቋሚያ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የሥራ መሪዎች ላይ ሁኔታው በሚያስገድድበት ጊዜ ንብረቱ ወይም ከፍሉ ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል እንዲፈጸምበት ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

3/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተጠቀሱትን ተግባራት ሊፈፅሙ የሚችሉት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ውሳኔ ሲያስተላልፉ ብቻ ነው።

4/ ንብረቱ የተሰጠው ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ቢሆንም ይህ አንቀጽ ለበጐ አድራጐት ዓለማዎች በተሰጠ ንብረት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

5/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በኤጀንሲው ሲጸድቅ ብቻ ነው።

**98. የአነስተኛ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ልዩ ድንጋጌዎች**

1/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ በመጨረሻው የሒሣብ ዓመቱ ጠቅላላ ገቢው ከ50,000.00 ብር በላይ ካልሆነና የማይንቀሳቀስ ንብረት የያዘ ካልሆነ በስተቀር የበጐ አድራጐት ድርጅቱ የበላይ አካል የሚከተሉትን ሊፈጽም ይችላሉ፤

ሀ) የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ሁሉም ንብረቶች ለሌላ የበጐ አድራጐት ድርጅት እንዲተላለፍ ወይም እንዲከፋፈል፤

ለ) የመተዳደሪያ ደንቡ ሁሉንም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ዓላማዎች በጐ አድራጐት ወደሆኑ ሌሎች አላማዎች በመለወጥ እንዲሻሻል ማድረግ፤

ሐ) የበጐ አድራጐት ድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ማናቸውም ድንጋጌዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቱን በማስተዳደር ረገድ የስራ መሪዎች ከአስተዳደሩ ጋር በተያያዘ ሊከተሏቸው የሚገቡ ስነሥርዓቶች በተመለከተ እንዲሻሻል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማንኛውም ውሣኔ የሚተላለፈው በአደራ ጠባቂዎች ወይም በቦርዱ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ብቻ ነው፤

3/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በኤጀንሲው ሲጸድቅ ብቻ ነው፤

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ በንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ)-(ሐ) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንዲፈጽሙ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ሕዝባዊ መዋጮ

**99. ለሕዝባዊ መዋጮ ስለማመልከት**

1/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሕዝባዊ መዋጮ ማካሄድ የሚችለው በኤጀንሲው ሲፈቀድለት ብቻ ነው፡፡

2/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጥ ፈቃድ የሕዝባዊ መዋጮውን ዓላማ፣ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ቦታውንና ሌሎች በኤጀንሲው የሚወሰኑትን መመዘኛዎች መያዝ አለበት፡፡

3/ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን ተላልፎ የተሰበሰበው ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት በኤጀንሲው ሊወሰድና ለተመሳሳይ በጐ አድራጐት ወይም ማህበር ዓላማ እንዲውል ሊደረግ ይችላል፡፡

**100. በማመልከቻ ላይ መወሰን**

1/ ሕዝባዊ መዋጮ ለመሰብሰብ ማመልከቻ ሲቀርብ ኤጀንሲው አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ፈቃዱን በገደብ ወይም ያለገደብ መስጠት ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል፤

2/ ኤጀንሲው ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገ ወይም በፈቃዱ ላይ ማናቸውንም ገደብ ሲያደርግ ለማመልከቻ አቅራቢው ውሣኔውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

**101. የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሚያስከለክሉ ምክንያቶች**

ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ ሊከለክል ይችላል፤

1/ ሕዝባዊ መዋጮው ለበጐ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ለማህበሩ ዓላማ የሚውል ካልሆነ፤

2/ በአመልካቹ የቀረበው ማስረጃ ሐሰኛ ወይም አሳሳች ከሆነ፤

3/ ሕዝባዊ መዋጮውን የሚያከነውኑት ሰዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 71 የተደነገጉትን መመዘኛዎች የማያሟሉ ከሆነ።

**102. ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድን ስለመሠረዝ**

1/ ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፤

ሀ) ፈቃዱ ከተሰጠ በኋላ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 112 ድንጋጌዎች እንዳልተሟሉ ሲረጋገጥ፤

ለ) ሕዝባዊ መዋጮው ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እንዲተዳደር የተደረገ ሲሆን፤

ሐ) ፈቃዱ ሲሰጥ በኤጀንሲው የተጣለው ገደብ የተጣሰ ሲሆን።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድ ሲሰረዝ የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት በኤጀንሲው ተወስዶ ለበጎ አድራጎት አላማ ሊሰጥ ይችላል።

## ክፍል አሥር

## ቅጣቶች

**103. ጠቅላላ**

1/ በዚህ ክፍል የተደነገጉት የወንጀል ድርጊቶች በበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት ከበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ ሥራ ጋር በተያያዘ የስራ መሪው ወይም ሰራተኛው የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን አላግባብ በመሣሪያነት በመጠቀም ከሆነና በማናቸውም ምክንያት በበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ላይ የሚሳበብ ከሆነ ነው።

2/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ መቀጣት የስራ መሪዎች ወይም ሰራተኞች በየግላቸው ላደረጉት ወንጀል ሊወሰንባቸው የሚገባውን ቅጣት አያስቀርም።

**104. ሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት**

1/ ማንኛውም ሰው ወይም የሰዎች ስብስብ በዚህ አዋጅ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይመዘገብ እንደ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሲሰራ ቢገኝ ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ሳያጸድቅ ሲሠራ ቢገኝ ሕገ-ወጥ በጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር እንዳቋቋመና በዚያም ውስጥ እንደተሳተፈ ይቆጠራል።

2/ በማንኛውም ሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የማስተዳደር ሥራ ውስጥ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከብር 10,000.00 በማያንስ እና ከብር 20,000,00 ባልበለጠ መቀጮ እና ከ5 አመት በማያንስና ከ15 ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

3/ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ውስጥ አባል የሆነ ወይም እንደ አባል የተሳተፈ ወይም በሕገ ወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ስብሰባ ላይ የተገኘ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከብር 5000.00 በማያንስ እና ከብር 10,000.00 ባልበለጠ መቀጮ እና ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ10 አመት ባልበለጠ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

4/ ማናቸውም ሰው ለአንድ ሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር በልገሳ ወይም አስተዋጽኦ ለማበርከት ቃል በመግባት ወይም በአባልነት ክፍያ መልክ ወይም በማናቸውም መንገድ ገንዘብ ወይም ንብረት የሰጠ ወይም

ከማናቸውም ሌላ ሰው ያስገኘ ወይም ለማስገኘት የሞከረ እንደሆነ በአባሪነት ይቀጣል፡፡

**105. በቅጥር ግቢ ውስጥ ሕገ-ወጥ ስብሰባ ስለማካሄድ**

ማንኛውም ሰው እያወቀ የእርሱ በሆነ፣ በይዞታው ስር ባለ ወይም በሚቆጣጠረው ቤት፣ ህንፃ ወይም ቦታ የሕገ ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም አባላቱ ስብሰባ እንዲካሄድ የፈቀደ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከብር 2000.00 ባላነሰ እና ከብር 5,000.00 ባልበለጠ መቀጮ እና ከ2 ዓመት ባላነሰ እና ከ5 አመት ባልበለጠ እሥራት ይቀጣል፡፡

**106. ሕገ-ወጥ መዋጮና ገቢ መሰብሰብ**

ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ሕዝባዊ መዋጮ የሰበሰበ ወይም በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ ከተሠማራ በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከብር 5000.00 በማያንስ እና ከብር 10,000.00 ባልበለጠ መቀጮ እና ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ10 አመት ባልበለጠ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

**107. የሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅትን ወይም ማሕበርን መረጃ ማሰራጨት**

ለአንድ ሕገ-ወጥ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ጥቅም መረጃን ያተመ፣ ያሳተመ፣ ለእይታ ያቀረበ፣ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ በፖስታ ወይም በማናቸውም የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ያስተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከብር 3000.00 ባላነሰ እና ከ5,000.00 ብር ባልበለጠ መቀጮ እና ከ2 ዓመት ባላነሰ እና ከ5 አመት ባልበለጠ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘበት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ማናቸውም መጽሐፍ፣ በየጊዜው የሚወጡ የህትመት ውጤት፣ በራሪ ወረቀት፣ ፖስተር፣ ጋዜጣ ደብዳቤ ወይም ሌላ ማናቸውም ሠነድ ወይም ጽሁፍ ይወረሳል፡፡

**108. ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ስለመጠት**

1/ ማንኛውም ሰው በቸልተኛነት ለኤጀንሲው ወይም ለዘርፍ አስተዳዳሪ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ የሰጠ እንደሆነ የወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከብር 5,000.00 በማያንስ እና ከብር 10,000.00 ባልበለጠ መቀጮ ወይም በቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

2/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ለኤጀንሲው ወይም ለዘርፍ አስተዳዳሪ ማስረከብ ያለበትን ማናቸውንም ሠነድ ሆን ብሎ የለወጠ፣ የሸሸገ፣ የደበቀ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፣ ወይም ሆን ብሎ ለኤጀንሲው ወይም ለዘርፍ አስተዳዳሪ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ የሰጠ እንደሆነ በወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከብር 10,000.00 በማያንስና ከብር 15,000.00 ባልበለጠ መቀጮ እና ከ5 ዓመት ባላነሰና ከ10 ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**109. የገቢ ማስገኛ ስራዎች**

1/ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ከኤጀንሲው በጽሁፍ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ለበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አባላት ወይም ተጠቃሚዎች ሊከፋፈል የማይችል እና ገቢው ለዓላማው ማስፈጸሚያ የሚውል ከአላማው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ገቢ የማመንጨት ሥራዎች ሊያከናውን ይችላል፡፡

2/ ገቢ የሚያስገኙ ስራዎችን የሚሰራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎቹን በተመለከተ የተለዩ የሂሣብ መዛግብት መያዝ አለበት፡፡

3/ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ትርፉን ለአባላቱ አከፋፍሎ ወይም የተለየ የሂሣብ መዛግብት ሳይይዝ ቢገኝ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 94 መሰረት አግባብነት ያለውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

4/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሌሎች ሕጎች ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ሌሎች ትርፍ ለማግኘት የሚሰሩ ሥራዎችን ምዝገባና ፈቃድ በሚመለከት የተደነገጉትን መስፈርቶችና ሥነ ሥርዓቶች አያስቀሩም፡፡

**110. <u>አቤቱታና ይግባኝ</u>**

1/ ኤጀንሲው ማንኛውንም በአሰራሩ ላይ የሚቀርብለትን አቤቱታ ተቀብሎ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ መወሰን አለበት፤

2/ በማንኛውም ኤጀንሲው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅረታ ያለው ሰው ውሳኔው በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ቢኖርም የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ኢትዮጵያዊ በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው የሕግ ጥያቄን በሚመለከት ቦረዱ ውሳኔ በሰጠ 15 ቀን ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ መሰረት በይግባኝ ሂደት ላይ የሚገኝ የምዝገባ ወይም የስረዛ ጉዳይ ከሆነ የሚመለከተው አካል የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ እንዳልተመዘገበ ወይም እንዳልተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

**111. <u>ወንጀልን ስለመመርመርና ክስ ስለማቅረብ</u>**

1/ በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦች የተደነገገውን ማናቸውንም ወንጀል በተመለከተ የሚካሄድ የምርመራ ወይም የክስ የማቅረብ ሂደት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ይመራል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ኤጀንሲው ለወንጀል ክስ የሚረዱ ማናቸውንም ማስረጃ በማደራጀት ክስ የመመስረት ሥልጣን ላለው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

**112. <u>መዋሐድ</u>**

1/ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት አግባብነት ባላቸው ሕጐችና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በአዲስ ስም ወይም ከሚዋሃዱት በአንዱ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ስም ሊዋሐዱ ይችላሉ፡፡ ውህደቱ ሲፈጸም የቀድሞ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት መብትና ግዴታ ወደ ተዋሃደው ድርጅት ይተላለፋል፡፡

2/ የተዋሃደው አዲስ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለበት፡፡

**113. <u>መከፋፈል</u>**

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር የማቋቋሚያ ሠነዱ የሚፈቅድ ከሆነ እና አግባብነት ያለው አካል ከፈቀደ በሕግ መሰረት ሊከፋፈል ይችላል፡፡

2/ የተከፋፈሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት የቀድሞ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ላለበት ግዴታ ሃላፊና የመብቱ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ የሚተላለፉትን መብቶችና ግዴታዎች መጠን አግባብነት ባለው ሕገደንብ፣ በስምምነት ወይም በሕግ ይወሰናል፡፡

3/ የቀድሞው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሕልውና የሚያበቃው ለአዲሶቹ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲሰጥና የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡

4/ በሁሉም አዲሶቹ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት ስምምነት ከነሱ አንዱ የቀድሞውን የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ስም ይዞ እንዲቀይ ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**114. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**115. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**116. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

1/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ ይህን አዋጅ እስካልተቃረነ ድረስ ይቀጥላል፡፡

2/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ተመዝግቦ የነበረ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና መመዝገብ አለበት፡፡

**117. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ---------- ቀን 2000 ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት